# በሁሉም ሃይማኖቶች ተከታዮች የኅብረት ትግል ወያኔን ለማስወገድ ቆርጠን እንነሳ

የግንቦት 7 ድምጽ ቁጥር 60 ርዕሰ አንቅጽ

ሰሞኑን በደሴ ከተማ ወገኖቻችን ላይ የደረሰው አሰቃቂ ጭፍጨፋ፣ የአካል ጉዳትና ሽብር ከዚህ ቀደም *‹‹የመለስ ዜናዊን የአጥፍተህ ጥፋ ሴራ ማምከን የሁሉም ኢትዮጵያዊ የዜግነት ግዴታ ነው››* በሚል ርዕስ በቁጥር 49 ጋዜጣችን ርዕሰ አንቀጽ፣ በሌሎች በርካታ የግንቦት ሰባት ጽሁፎች እና የጉባዔ ውይይቶች አንስተነው ወደነበረው ወያኔ በሃይማኖት ሰበብ በሕዝባችና አገራችን ላይ ስለሚያደርሰው በደል እንደገና እንድንመለስበት አድርጎናል።

ከሁሉ አስቀድመን በአረመኔው የወያኔ ጥይት ውድ ሕይታወቸው ላጡ ወገኖቻችን የተሰማንን ጥልቅ ሃዘን እየገለፅን ለቤተሰቦቻችውና ለሁለቱም ሃይኖቶች ምዕመናን መጽናናትን እንመኛለን። እንደዚሁም ለተለያዩ የአካል ጉዳቶች እና ሰቆቃዎች ለተዳረጋችሁ ወገኖቻችን ህመማችሁ ህመማችን፤ ቁጭታችሁ ቁጭታችን መሆኑን በጥልቅ ሃዘን ስንገልጽ ይህንን ሰቆቃ የነደፉ፣ የፈቀዱና ያካሄዱ የወያኔ ሹማምንትና ሎሌዎቻቸው ለፍርድ የሚቀርቡበትን ጊዜ ለማሳጠር ጠንክረን እየሠራን መሆኑን እናረጋግጣለን።

ኢትዮጵያ ተቀራራቢ ቁጥር ያላቸው ሙስሊምና ክርስቲን ዜጎች ያሏት መሆኑን፤ ሁለቱ ሃይማኖቶች ተከባብረው ሙስሊሙ የክርስቲያኑ፣ ክርስቲያኑ ደግሞ የሙስሊሙን በዓል የሚያከብርበት አገር እንደሆነች፤ ይህ ባህል የኢትዮጵያ ክብር መሆኑ፤ ሙስሊምና ክርስቲያን ተደጋግፎ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መፍጠር ከቻለ ለአፍሪቃ ቀንድ ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም ትልቅ ትምህርት ሰጭ ተግባር ሊሆን እንደሚችል ግንቦት ሰባት ከላይ በተጠቀሰው ርዕሰ-አንቀጽ፣ በሌሎች ጽሁፎችና ባካሄዳቸው ጉባዔዎች በተደጋጋሚ ገልፆዓል። ወያኔ ኢትዮጵዊያንን በዘር ለመከፋፈል ሞክሮ የጠበቀውን ያህል ውጤት ባለማግኘቱ ሃይማኖትን በተጨማሪ መሣሪያነት ሊጠቀም መወሰኑን በተግባር እያሳየ መሆኑን በጅማ፤ በሃረር፣ በአዲስ አበባ እና ጎንደር የታዩትን ምልክቶች በመጠቃቀስ ተችቶባቸዋል። በሃይማኖት ሰበብ የሚነሳ ቅራኔ በዘር ሰበብ ከሚነሳ ቅራኔ የባሰ አውዳሚ እና በቀላሉ ድንበር ተሻጋሪ መሆኑን በመገንዘብ ሁላችንም ይህንን መሰሪ ተግባር ነቅተን እንድናከሽፍ ግንቦት ሰባት ጥሪ ሲያደርግ ቆይቷል።

የወያኔ ሃይማኖትን ለእኩይ ግቡ የመጠቀም መሰሪ ተግባር ደሴ መዝለቁ የጉዳዩን አሳሳቢነት አጉልቶ ያሳያል። እንደሚታወቀው ወሎ የእስልምናና ክርስትና ሃይማኖቶች ከመቻቻልም አልፎ መፋቀር የሚችሉ መሆኑን ማስመስከር የቻለች ነች። በወሎ በተለይም በደሴ ዙርያ ክርስቲያኑና ሞስሊሙን በስምም ይሁን በባህሪይ መለየት እስከማይቻል ድረስ የተቀራረቡ ናቸው። ከፊል አባላቱ ክርስቲያን፤ ከፊሉ ደግሞ ሞስሊም የሆነባቸው ቤተሰቦችን በመያዝ ደሴ ዙሪያ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ከመላው ዓለም ቀዳሚ ናት። አሁን የጭፍጨፋው ሰበብ የሆነው የአርሴማ ቤተክርስቲያን ግንባታ ጉዳይ ከእስከዛሬዎቹ የወያኔ ትንኮሳዎች ሁሉ የባሰ መርዛማ ያደረገው በወሎ መደረጉና ዓይን ባወጣ መንገድ የሁለቱን ሃይማኖቶች ተከታዮች ለማጋጨት የታለመ በመሆኑ ነው።

ይህ የወያኔ አሳፋሪ የተንኮል ታሪክ ባጭሩ የሚከተለው ነው። ለደሴ አርሴማ ቤተክርስቲያን ግንባታ በተጠየቀው መሬት ላይ የከረረ የሞስሊሞች ተቃውሞ አልነበረም፤ መለስተኛ ቅሬታዎችም የሃይማኖት አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች ከሁለት ዓመት በፊት ተነጋግረው

ጨርሰውት ቤተክርስቲያኒቷም ለሁለት አመታት በዚሁ ቦታ በድኳን ውስጥ አገልግሎት ስትሰጥ ቆይታለች።

ሲያሻው መሬት በመስጠት አሽከሮቹን ሚሊነር ማድረግ፤ ጥቅማቸው ሲያበቃ ደግሞ የሰጠውን መሬት በመቀማት በቅጽበት ወደ ቀድሞ ድህነታቸው በመመለስ የተካነው ወያኔ መሬት ለመስጠትም ሆነ ለመንፈግ ምክንያት መስጠት አያሻውም። ወያኔ የአርሲማን ቤተክርስቲያን ይዞታ ለካድሬዎቹ ማደል ፈልጎ ከሆነ ይህንኑ መንገር የሚከለክለው የለም። ከፈለገም በመከረኛው ‹‹ልማት›› በማሳበብ ‹‹ቦታውን ለልማት እፈልገዋለሁ›› ማለት ይችል ነበር። ወያኔ የአገሪቷ መሬት ብቸኛ ባለንብረት መሆኑ ለእንዲህ ዓይነት እኩይ ተግባር እየተጠቀመበት መሆኑ አገር ያወቀው ሃቅ ነቅ። እናም ይኸ ሁሉ አማራጭ እያለ ‹‹መሬቱ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ያልተፈቀደው ሞስሊሞች ስለተቃወሙት ነው›› ብሎ ማስወራት እንደምን ያለ አስነዋሪ ተግባር ነው? ለምንስ ይኸንኑ ምላሽ ለሠላማዊ ሰልፈኞቹ በኦፊሴል አልሰጠም? የከተማው አስተዳደር ተብየው ለሰላማዊ ሰልፍ ፈቃድ ሲሰጥ የሰልፈኞቹ ጥያቄ ምን ሊሆን እንደሚችል አልገመተም ነበር ይሆን?

የሰላማዊ ሰልፈኞቹ ጥያቄ ግልጽ ነበር፤ በማመልከቻቸውም በግልጽ ሰፍሯል። ምዕመናኑ ለከተማው አስተዳደር ያቀረቡት ተደጋጋሚ ጥያቄ ምላሽ በማጣቱ የተጠራ ሰልፍ ነበር። ሆኖም ሳይመረጥ የከተማው አስተዳደር ነኝ ብሎ ራሱን የሰየመው የወንበዴው አካል የሕዝብን ጥያቄ ለማስተናገድ ፈቃደኛ አልነበረም። አቤቱታ ለመስማት የፈቀደ አንድም ባለሥልጣን አልተገኘም። ሰልፈኛው በምክር ቤቱ በራፍ ላይ በነበረበት ጊዜ ባለሥልጣናቱ በስልክ እየተነጋገሩ የነበረው ከባህርዳር ፈጥኖ መድረስ ስለሚኖርበት ገዳይ ሠራዊት ብዛት ነበር። ሰልፈኛው ምላሽ ሲያጣ ለአቤቱታው ራሱ ውሳኔ ሰጠ - ሕዝባዊ ውሳኔ። እናም ሰልፈኛው በራሱ ውሳኔ ግንባታው ያጣድፈው ገባ። ገዳይ ሠራዊት ሌላ አገር ቢሆን ኖሮ ለጦርነት እንጂ በአድማ መበተኛነት ሥራ ላይ የማይውሉ መሣሪያዎችና ጥይቶች ታጥቆ ተላከና ደረሰ። ወደ ሰማይ፣ ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ ሳይሆን በቀጥታ በሥራ ወደተጠመዱት ምዕመናን ተኮሰ። እናቶች፣ አባቶች፣ ወጣቶች ጮሁ፤ ሰሚ አልነበረም። አልሞ ተኳሾች ከሃያ በላይ የሚሆኑትን አነጣጥረው ጣሉ ከእነዚህም ሶስቱ ወዲያኑ ሕይወታቸው ሲያልፍ ሁለቱ ደግሞ ሆስፒታል ደርሰው ለዘላለሙ አሸለቡ፤ ቀሪዎቹ ለአካል ጉዳት ተዳርገው በስቃይ ላይ ይገኛሉ። እስቲ ይኸንን ውንብድና ምን ይሉታል?

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!!! የወያኔ መሰሪ መቅበጥበጥ የመጨረሻው ጣራ መድረሱን ልብ በል። አንዴ የመነኩሴዎችን ካባ እየለበሰ ነቢዩ መሐመድን በአደባባይ በመዘለፍ ሞስሊሞችን በክርስቲያኖች ላይ ያነሳሳል። ሌላ ጊዜ ደግሞ በደሴ እንደታየው ሞስሊሞች ስለተቃወሙ ለቤተክርስቲያን መሬት መስጠት አልቻልኩም ብሎ ክርስቲያኖችን በሞስሊሞች ላይ ያነሳሳል።

ለወያኔ ትንኮሳ የደሴ ሞስሊም ማኅበረሰብ በሰጠው ‹‹እኛ ተቃውመን አናውቅም ምላሽ›› ወያኔ ምን ያህል እንዳፈረ መገመት ቀላል ነው። እንዲህ ዓይነት ዓይን ያወጡ ትንኮሳዎች በደሴም በሌሎችም ቦታዎችም መቀጠላቸው አይቀርም ምላሻችን እንደ ደሴ ሞስሊም ወንድሞቻችን ‹‹አንጣላልህም፤ ይልቁንስ የችግሮቻችን ምንጭ አንተ ነህና ወጊድ!›› የሚል መሆን ይኖርበታል።

ይህንን ከፋፋይ ሥርዓት ለማስወገድ በኅብረት መነሳትን ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ አጣዳፊ ጉዳይ ነው። በሁሉም የአገራችን ሃይማኖቶች ተከታዮች ፍቅርና የኅብረት ትግል ወያኔን አስወግደን ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ የሰፈነባት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ቆርጠን እንነሳ።